# የዝምታ ዝማም

ቤተ ክርስቲያን ስትበላሽና ሐሰት ሲሠለጥን
ታላላቆችና መሪዎች ለምን ዝም አሉ?

ዘላለም መንግሥቱ

**ዝማም ፤ (ማች) ፤ ዝምታ ፥ አርምሞ ። ታናሽ ፥ ቅርጫት ፥ እንደ ፥ ከረጢት ፥ ኹኖ ፥ የእንስሳን ፥ አፍ ፥ የሚ ከት ፤ መንግን ፥ በመያዝና ፥ በማሰር ፥ ፈንታ ፥ የሚደረግ ። ትግሣጽ ፥ ወትምህርት ፥ ልጓም ፥ ወዝማም ፥ (ፈላስ) ። —፤ ንፎ ፥ መንደልት ፤ ያፍንጫ ፥ ቀለበት ፥ የአራዊትና ፥ የእንስሳት ፥ ስናግ ፤ ገመድ ፥ እያበቱ ፥ የሚስቡበት ። ት ወዲ ፥ ሎቱ ፥ ዝማማተ ፥ ውስተ ፥ አንፉ ። እወዲ ፥ ለከ ፥ ዝማማተ ፥ ውስተ ፥ አንፍከ ፥ (ኢዮብ ፥ ፷ ። ኢሳ፴፯ ፥ ፳፱) ። ወጸበን ፥ እይ ።**



**ዝማም ፥**

ኪዳነ ወለዱ ክፍሉ፤ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላተ ሐዲስ፤ ገጽ 423።

# የዝምታ ዝማም

የአገራችን ወንጌላዊ ክርስትና ሲጠለፍና ሲደፈር፥ ሲቀየጥና ሲለወጥ፥ ሲሰበርና ሲበየድ፥ ሲሸረፍና ሲጎመድ፥ ታላላቆች የሚባሉ፥ መሪዎች የሚባሉ ለምን ዝም አሉ? ለምን አደብ ገዙ? ለምን ተባበሩ? ብለን ጠይቀን እናውቃለን? አባቶች የተባሉ፥ አንቱ የተባሉ ለወንጌል ዋጋ ከፈሉ የተባሉ፥ ከፈልን ያሉ፥ የታሰሩና የተፈቱ የተባሉ፥ ታስረን ተፈታን ያሉ፥ 'በንጉሡ ዘመን እንዲህ ነበር፤ በደርግ ዘመን እንዲህ ነበር እያሉ የሚነግሩን፥ 'የጠራው ክርስትና፥ ወንጌላዊ ክርስትና እንዲህ ነበር፤ ክርስቶስን መምሰል እንዲህ ነበር፤ እያሉ የነገሩን፥ ዛሬ ክርስትና ሲበከል፥ ሲረክስ ለምን ዝም አሉ? ለምን አፋቸው ላይ ዝማም ኖረ? እንዴት አስቻላቸው? እንዴት ቻሉት? ወይም እንዴት ቻሉበት? አንዳንዶች እንዲያውም በግልም ተጠይቀዋል፤ 'አንተ ብትናገር እኮ ትደመጥ ነበር፤ ትደመጣለህ፤ እባክህ አንድ በል' ተብለዋል። ግን መልሳቸው ዝምታ ነው።

አዲሱ ትውልድ ያንን ወይም የቀድሞውን ወይም ትክክለኛውን ወንጌላዊ ክርስትና ባያውቁ ይሆናል የተሳሳቱት እንበልና፥ ያወቁትስ? ያወቁት ምን አደረጉ? ዝምታ ለምን ሰፈነ? ዝምታው ለምን ገዘፈ? ሲጀመር ለምን ዝም አሉ? ቀጥሎ፥ ዝምታቸውን መስበር ስለምን አልቻሉም? ምክንያት አላቸው። በኔ ግምት ለዚህ ዝምታቸው ምክንያቶች ናቸው የምላቸውን ጥቂት ዋና ዋና ነጥቦች አካፍላለሁ።

1ኛ፥ ደንታቢስነት ወይም ግድ የለሽነት። ዛሬ በጌታ ቤት የሚሆነው ነገር፥ በወንጌላዊ ክርስትና ላይ የሚሆነው ነገር ምንም ደንታ የማይሰጣቸው፥ ምንም ግድ የማይሰማቸው ሰዎች አሉ። ይህ ደንታቢስነታቸው የሚያሳየው ምንድር ነው ቢባል፥ ቀድሞም በጤናማ ወንጌላዊ ክርስትና ውስጥ ሁኔታው ምቹ ሆኖላቸው ተገኙ እንጂ፥ ባይሆንም ኖሮ ምንም ግድ አልነበራቸውም ማለት ነው። እነዚህ ቤቱ ቢገማ፥ ቢረክስ ምንም ስሜት የማይሰጣቸው ናቸው። ግድ የለሾች፥ ደንታቢሶች።

2ኛ፥ ፍርሃት ወይም ፈሪነት። ፍርሃት ዓይነቱና ምንጩ ብዙ ነው። የሰው ፍርሃት ሊሆን ይችላል፤ የባለ ሥልጣን ወይም የመንግሥት ሊሆን ይችላል፤ ከወዳጆች የመገለልና የመገፋት፥ ወደ ጎን የመደረግ፥ ገሸሽ የመደረግ ፍርሃት ሊሆን ይችላል፤ ፈቃዴን እነጠቅ ይሆን? መብቴን አጣ ይሆን? የሚል ፍርሃት ሊሆን ይችላል፤ ሌላውን ማስቀየም የሚያመጣውን ጠንቅ መፍራት

ሊሆን ይችላል፤ ሌሎችም ፍርሃቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ብቻ ፍርሃት ሐሰተኞችን፥ በካዮችን እያዩ ዝም የሚሉበት ፍርሃት ነው። ፍርሃት ዝም ያስብላል።

3ኛ፥ ዝምተኝነት ወይም ራሱ ዝምታ። ዝምታን መምረጥ፤ ዝምታ ወርቅ ነው እንደሚሉት። እንዳማረብኝ፥ ሳልነካካ፥ ማንንም ሳልነካ፥ ማንንም ስላስቀይም፥ ባለሁበት አጥቢያ ልኑርበት፤ ስሜን ጠብቄ፥ በተከበርኩበት ክብሬን ጠብቄ ልኑርበት። በመደገፍ የሚገኝ ጥቅምም ይቅርብኝ፥ በመንቀፍ የሚገኝ ጉዳይም ይቅርብኝ፤ ሁለቱም ይቅርብኝ፤ ነመን በጤና የሚሉ ናቸው ዝምታን መራጮች።

4ኛ፥ ጥቅመኝነት ወይም ጥቅመኞች። ጥቅምን በተመለከተ ፍርሃት ባልኩበት ዓይነቱና ምንጩ ብዙ ነው እንዳልኩት ይህም እንደዚያ ነው። እዚያ አስፈራሪ የሆኑት ነገሮች እዚህ ደጓሚና አጉራሽና ጠቃሚ መሆናቸው አንዱ ገጽታ ነው። ለምሳሌ፥ እዚያ አስፈራሪው ባለ ሥልጣን ቢሆን፥ እዚህ ጠቃሚውና ደጓሚው ያው ባለ ሥልጣን ሊሆን ይችላል። እዚያ አስፈራሪው ቆንስላው ቢሆን፥ እዚህ ጠቃሚው ይሆናል። እዚያ አስፈራሪው ግለ ሰብ ከሆነ እዚህ ጥቅም ሰጪው ያው ግለ ሰብ ሊሆን ይችላል። ሌላው የጥቅም ገጽታ የጥቅም መቅረት ገጽታ ነው። 'ብናገር፥ ብገስጽ፥ ብዘልፍ፥ ብቆጣ፥ ጉዳት ሊደርስብኝ ይችላል፤ ጥቅም ሊቀርብኝ ይችላል፤ ከሥራ ልባረር፥ ከአገልግሎት ልታገድ እችላለሁ፤ ዕድሜዬ እየገፋ ነው፤ እንዴት እኖራለሁ፤ ለአገልግሎት ከመጋበዝ ልሰረዝ እችላለሁ፤ ካልተጋበዝኩ የፍቅር ስጦታና ጥቅማ ጥቅም ይቀርብኛል፤ በተለይ የአገልግሎት ግብጥው ውጪ አገር ከሆነ መናገር ለምን ጥንቅር ብሎ አይቀርም፤ አላደርገውም።' ይህ የጥቅመኝነት ጉዳይ ነው። ጥቅም ዝም ያሰኛል።

5ኛ፥ ማመንና መደገፍ ወይም ደጋፊነት። አንዳንዶቹ ይህንን እየተጠለፈና እየተደፈረ ያለውን ወንጌላዊ ክርስትና የሚጠልፉት ሰዎች፥ እነዚህ ሐሰተኞች ሰዎች ሐሰተኞች እንዳልሆኑና ትክክል እንደሆኑ ያምናሉ፤ አማኞች ናቸው። ወይም አዛኝ ወጋኝ ደጋፊዎች ናቸው። ይህንን እየሆነ ያለውን ትርምስ፥ ቤተ ክርስቲያንን፥ ወንጌላዊ ክርስትናን እያቆሸሸም፥ እያሳሳቀም እየወሰደ ያለውን ማዕበልና ጎርፍ ይወድዱታል፤ ይደግፉታል። ጋሽ በቄ፥ በቀለ ወልደ ኪዳን ሐሰተኛ ነቢይ ኢዩ ጩፋን፥ 'ሐሰተኛ ነው' ማለት አይችልም። እንደ እርሱ ያሉትን ሲናፍቅና ሲጠብቅ ለዓመታት ኖሮአል። ቄስ በሊና ሲቀባቸው የኖሩትን ሐሰተኞች ስተዋል አላለም፤ ያንን ለማለትም ዕድል ሳያገኝ ሆዶአል። እነዚህ ሰዎች እነዚህ ሐሰተኞች

የእግዚአብሔር ሰዎች እንደሆኑ ያምናሉ። ስለዚህ ደግፏቸዋል። ዳዊት ሞላልኝ ሐሰተኛ ነቢይ በላይ ሽፈራውን፥የሐሰት ትንቢቶቹን እያየም፥ እየሰማም ‘ሐሰተኛ ነው’ ማለት አይችልም። የቀባው እርሱ ነዋ! ያምንበታላ! ያንን ጅግ ሙሉ ዘይት የደፋበት እርሱ ነዋ! ያምኑባቸዋል፤ ይሳሱላቸዋል፤ ይደግፏቸዋ። ይህ 5ኛው ነጥብ ነው። ደጋፊነት።

6ኛ፥ ጎራሽነት። የጎረሱት ጉርሻ አላናግር ያላቸው ወይም ዝም ያሰኛቸው ሰዎች ደግሞ አሉ። ይህኛው ከላይ ጥቅመኞች ካልኳቸው ጋር ይቀራረባል። ቢቀራረብም፥ ግን የተለየም ነው። ሐሰተኞች ነቢያትና ሐዋርያት ሰው ይመርጡና ያንን ሰው ያጎርሱታል። የጎረሰ አፍ ደግሞ እንደሚታወቀው መናገር አይችልም። ጎርሶ መነፋነፍ እንጂ መናገር አይቻልም። በጎረሰ አፍ ሲናገሩ ወይ ትንታ ይይዛል፤ ወይም የበላነው ይንጠባጠባል፤ ለማየት ደስ አይልም።

ሐሰተኛ ነቢይ ሱራፌል ደምሴ ወደ ሆሳዕና ሄዶ በፈረንጆች 2017 እርሱ መርዙን በዘራ በሳምንቱ እዚያ ነበርኩና የቃለ ሕይወት አባቶች ከተባሉት ጥቂት መርጦ፥ ይህ ሸንጋይ፥ እነሱን ባርኩኝ ብሎ ተንበርክኮ ባርከውት፥ በእጆቻቸውም የሆኑ ነገሮቹን አስጨብጧቸው፥ ሲባርኩት ሲመርቁት የሚያሳይ ቪድዮ አውጥቶ ለቀቀ። ባርኩኝ፥ መርቁኝ ሲል ይህ አጭበርባሪ አስልቶ ነው። እነዚያ መራቂዎች ወይ በጉርሻው ተደልለዋል፤ ወይም የዋሆች ናቸው። ኮንፈረንሱ ላይም ከፊት ተርታ ምቹ ወንበር ላይ አስቀምጧቸው ያም ታየ። የቃለ ሕይወት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ወጣቶቻቸውን አትሂዱ ቢሉ ምን ዋጋ አለው! ማን ይሰማቸው? ‘እንዴ? አባቶቻችን፥ እነ ጋሽ እንትና እነ አባባ እንትና የባረኩትን ሰው እኛ ምን ብለን ነው የምንቃወመው? ነበር ያሉትና ሄደው የተካፈሉት። አሁን እነዚያ አባቶች ሐሰተኛ ነቢይ ሱራፌል ሐሰተኛ ነው ማለት ይችላሉ? አይችሉም፤ ጎርሰዋላ!

ሐሰተኛ ነቢይ በላይ ሽፈራው ለቄስ ዓለሙ ሼጣ አዳራሹ ጋብዞ ከፊት አስቀምጦ ወደ መድረክ ጠርቶ መኪና ሸለመ። ይህንን ጉርሻ የጎረሰው የቄሱ አፍ በላይ ሽፈራው ሐሰተኛ ነው ብሎ መናገር ይችላል? አይችልም።

ሰርጉን ድል አድርጎ የደገሰለትን ወይም ለሰርጉ ወጪ መሸፈኛ ብሎ 150 ሺህ 200 ሺህ የሰጠውን ባለውለታ በሰርጉ ማግስት እንዴት ብሎ ነው፥ ‘ይህ ሐሰተኛ ነቢይ ወይም የሐሰት አስተማሪ ነው’ የሚለው? ይህ የአጉራሽ ነካሽ መሆን አይደለም እንዴ? ነው እኮ! ጎራሾች ይጎርሳሉ እንጂ አይተኩሱም። ጎራሽነት ዝም ያሰኛል።

7ኛ፥ ማዕረግተኝነት። ለማዕረግ፥ ለስም፥ ለክብር ተብሎ ዝም ማለት። መጋቢ ወይም ፓስተር ስለተባሉ፥ ያንን ሹመት ከነ ሙሉ ክብሩና ሥልጣኑ ለመጠበቅ ዝም ማለት፤ ወይም ከተናገሩ ከሚያገለግሏቸው ምእመናን የሚያኮርፉ ስለሚኖሩ እነዚያን ላለማስኮረፍ ዝም ማለት። ለማዕረግ። የዚህ ኮሌጅ ዲን ወይም ዲሬክተር፥ የዚህ ሚኒስትሪ መሥራች ወይም CEO ወይም ፕሬዚደንት ስለሆንኩ፥ ነገሩ ባይጥመኝም፥ መናገሩ አይመጥነኝም፥ ዐዛባ መዛቅ እኔን አይመጥንም፤ አይመስለኝም ብሎ ዝም ማለት። ራሳቸውን የከበረ ማማ ላይ አስቀምጠው ከዚህ ነገር በላይ ነን ብለው ራሳቸውን ስለሚቆልሉ ማዕረግተኞች ዝምታን ይመርጣሉ። አሳዛኙ ነገር፥ ሐሰተኞቹ ሐሰተኞች መሆናቸውን ልባቸው እያወቀው እንደዚህ የሚያደርጉትንም የሚያብጠለጥሉ ደግሞ አሉ። በአንድ ወቅት፥ ያንን ማዕረግ ከመቀዳጀታቸው በፊት እነሱም ስለታም የሐሰተኞች ነቃፊዎች ሆነው ኖረው አሁን ቆጥ ላይ ሲወጡ ወንበር ጠባቂ፥ ዙፋን ጠባቂ፥ የራሳቸው ወንበር፥ የራሳቸው ዙፋን ጠባቂ ይሆናሉ። ማዕረግተኝነት ዝም ያሰኛል።

8ኛ፥ ገማልያላውያን/ገማልያላዊነት። እነዚህ ቀደም ሲል ዝምተኝነት ካልኳቸው ጋር ይቀራረባሉ ግን የተለዩ ናቸው። እነዚህን ከነዚያ የተለዩ የሚያደርጋቸው፥ እንዲያው ዝም ማለት ሳይሆን፥ ፈርቶ ዝም ማለት ሳይሆን፥ ጎርሶ ዝምታም ሳይሆን፥ አምኖ ዝምታም ሳይሆን፥ ጠርጥሮ ዝምታ መሆኑ ነው። እርግጠኛ የአለመሆን ዝምታ ነው። 'ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ይሆን እንዴ? ምናልባት ከእግዚአብሔር ቢሆንስ? ከእግዚአብሔር ከሆነ ከእርሱ ጋር እንዳልጣላ ዝም ብል ይሻላል' የሚሉ ናቸው። ገማልያል ያለውን በሐዋ. 5 እናገኛለን። ቴዎዳስ ተነሥቶ 400 ሰዎች አስተባብሮ ታላቅ ነኝ አለ፤ ጠፋ፤ የገሊላው ይሁዳ ብዙ ሰዎች አስከትሎ ሸፈተ፤ ጠፋ። አሁንም እነዚህ ይጠፋሉ፤ ካልጠፉ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ ነበር ብሎ የመከረው። ይህ የሰውኛና የጥርጣሬ ምክር ነው።

9ኛ፥ መንግሥታውያን ዝምተኞች። እነዚህ ከመንግሥት መዋቅር ጋር የተቆራኙና በሙጫ የተጣበቁ ዝምተኞች ናቸው። ከኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ጠላፊዎች አንዱ መንግሥት መሆኑን ከዚህ በፊት ገልጫለሁ። መንግሥት ይህንን ያደረገው ቆንስላ የተባለ ጭራቅ በመፍጠር ነው። ቆንስላ የምለው የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች እብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ነው። እንግዲህ በቆንስላው በኩል ይሁን፥ በግል ግንኙነቶች ይሁን፥ በመሬትና በቦታ ስጦታ ወይም ሹመትና ሽልማት በኩል ይሁን ቁርኝት ከኖረ ያንን ቁርኝት ለመጠበቅ ሲባል ዝምታም ይኖራል። በዚህ ቁራኛ የተያዙ ሰዎች

መናገር አይችሉም፤ ዝምታን ይለብሱታል። ሐሰተኞችን ሐሰተኞች ናቸው ብለው መናገር አይችሉም።

ከላይ ያየናቸው ዘጠኝ ምክንያቶች በኔ መረዳት የደረስኩባቸው ናቸው። ከነዚህ የበዙና የከፉም ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እንግዲህ የዝምታ ዝማም በአፋቸው የተጣደባቸው ሰዎች ምክንያቶቻቸው ከነዚህ አንዱ ወይም ጥቂቱ ሊሆኑ ይችላሉ። የዝምታ ዝማም ያልኩት አፋቸው የተያዘ በመሆኑ ነው። ዝማም ማለት የሚያበራዩ ከብቶች ሲያበራዩ ወይም ሲወቁ እንዳይበሉ ወይም የሚጠቡ ጥጆች ከእናቶቻቸው ጋርም እየዋሉ እንዳይጠቡ አፋቸው ላይ የሚከደን መረብ ወይም የኬሻ ከረጢት ነው። አንዳንድ ተናካሽ ውሾችም አፍ ላይ ይደረጋል። ዝማም ለሰዎች ሲነገር አፍ እንዳይናገር መዝጊያ ማለት ነው። ዝማም ዝም ማስባያ፥ ዝም ማሰኛ ነው።

ሰው ሁሉ ስለሚናገርበት ስለ እያንዳንዱ ነገር መልስ እንደሚሰጥ በቃሉ ተጽፎአል። የዚህን ግልባጭ ነው እኔ የምለው ያለሁት። ሰዎች ስለሚናገሩት ብቻ ሳይሆን ስላልተናገሩበት ነገርም መልስ ይሰጣሉ። መናገር ሲኖርብን ስላልተናገርነው ነገርም እንጠየቃለን፤ መልስ እንሰጣለን። ሕሊናችን ሲጠይቅ ለሕሊናችን መልስ እንሰጣለን፤ ሰዎች ሲጠይቁ ለጠያቂዎች መልስ እንሰጣለን፤ ለእግዚአብሔርም መልስ እንሰጣለን። ታሪክም ይጠይቀናል፤ ለታሪክ መልስ መስጠት ግን አንችልም። ምክንያቱም ታሪክ ታሪክ የሚሆነው ይህ ነገር ካለፈ በኋላ ነው። ለታሪክ መልስ መስጠት ባንችልም፥ ጥያቄው ግን እየተንቀዋለለ ይኖራል፤ እንደተጠየቀ ጥያቄ ሆኖ ይኖራል። ተገድዶ መልስ ከመስጠት አስቀድሞ ዝም አለማለት እና መናገር አይሻልም? ለምን ዝም አልክ? ተብሎ ተጠይቆ ለዝምታው መልስ ከመስጠት መናገርን ራሱን መናገር አይሻልም? ይሻላል።